# የአክራሪነት እንቅስቃሴን መድፈቅ የሚያስችል ጉባኤ

ክፍል አንድ

**አዲስ ቶልቻ 09/06/13**

ባለፉ ሁለት አስርት ዓመታት በአረሲ፣ በባሌና በወሎ አካባቢ የኢትዮጵያ ነባረና ጥንታዊ የእስልምና ሃይማኖት አስተምህሮ ሃይማኖታዊ ስርአቶች የሚከወኑባቸው መስጊዶች ሲቃጠሉ፣ በኢትዮጵያ እስልምና እንዲስፋፋ ትልቅ አስተዋፅኦ ያበረከቱ መንፈሳዊ መሪዎችና የሃይማኖት አባቶች መቃብሮች እየተቆፈሩ አፅማቸው ሲቃጠል ቆይቷል፡፡

በተለያዩ አካባቢዎች አዲስ አበባን ጨምሮ አዛውንት የሃይማኖት መምህራን፣ የመስጊድ ኢማሞች በጥይት ተደብድበው፣ ከገደል ላይ ተወርውረው፣ በገጀራ ተጨፍጭፈው፣ ተገድለዋል፡፡ ወጣት ልጆች ከዋሃቢ ሰለፊ አስተምህሮ ውጭ የሆነ ሃይማኖታዊ ስርአት ይፈፅማሉ ያሉዋቸውን እናቶቻቸውን በጥይት ደብደበው፣ ጉድጓድ ውስጥ ከትተው ሕይወታቸውን አጥፍተዋል፡፡ የፀሎት ስርአት የሚፈፀምባቸው የተከበሩ መስጊዶች መጸዳጃ ተደርገዋል፡፡ በዚህም ምክንያት የነባሩ አሕለል ሱና የእስልምና አስተምህሮ ተከታይ ኢትዮጵያዊያን ለጭንቀትና ሰቆቃ ተዳርገዋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በባሌ ቡሳ ሰገል የተሰኘ ሁሴን ጃረሶ በተባለ ኬንያዊ የሚመራ የጀሃድ ቡድን፣ እንዲሁም  በደቡብ ወሎ ሃረከቱል ሸባብል ፊ ቢላል ሂጅራይተን የተባለ አማን አሰፋ ወይም ኢስማኢል በተባለ ግለሰበ የሚመራ የጀሃድ ቡድኖች ጦርነት ለመጀመር በመደራጀት ላይ ሳሉ ተደርሶባቸው እንዲጨናገፉ መደረጉ ይታወቃል፡፡ የሁለቱም የጀሃድ ቡድን መሪዎች የአልቃይዳ የአፍሪካ ክንፍ በሆነው አልሸባብ ተመልምለው የሰለጠኑ ናቸው፡፡

አዲስ አበባም ቢሆን በውጭ ሰልጥነው የመጡ የወሃቢ ሰለፊ መፈንጫነቱ አልቀረላትም፡፡ አዲስ አበባ አወሊያ መስጊድ ውስጥ የሙስሊሙን ሕጋዊ ጥያቄ ሽፋን አድርጎ የተነሳው “የሙስሊሞች መፍትሄ አፈላላጊ” በኋላም “ድምፃችን ይሰማ” የተሰኘው ስብስብ እስላማዊ መንግስት የመመስረት የሩቅ ግዜ እቅዱን ለማሳካት በውጭ ሰልጥነው በመጡ አክራሪዎች የሚመራ ነበር፡፡ ካሚል ሸምሱና አሕመድ ሙስጠፋ የተበሉ “የሙስሊም መፍትሄ አፈላላጊ” ወይም “ድምጻችን ይሰማ” የተባለ ስብስብ መሪዎች የነበሩ ወጣቶች ወደ ወጭ አገር በመሄድ ዶ/ር ጃሲም ሱልጣን በተባለ በሙስሊም ወንድማማቾች ፓርቲ ፖለቲካዊ አስተምህሮ የተቃኘ የቀለም አቢዮት ስልጠና ወስደዋል፡፡

በ1999 ዓ/ም በኦሮሚያ ክልል በጅማና ኢሉ አባቦር ዞኖች ወደግጭት ሊያመራ የሚችል ሆን ብሎ የተቀነባበረን ሰበብ መነሻ በማደረግ ካሃዋርጂያ በተባለ የዋሃቢ ሰለፊ የጀሃድ ቡድን በርካታ የኦርቶዶክስ ክርስትና ሃይማኖት ተከታዮች በአሰቃቂ ሁኔታ ተጨፍጭፈው ሕይወታቸው አልፏል፣ አካላቸው ጎድሏል፡፡ በ2003 ዓ/ም በጅማ ዞን በኦሞ ናዳ ወረዳ በተመሳሳይ ሁኔታ ለቁጣ ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉ ሁኔታዎችን ሆን ብሎ በመፍጠር የፕሮቴስታንት ክርስትና ተከታዮች ቤተ ክርስቲያኖንና መኖሪያ ቤቶች በእሳት ተቃጥለዋል፣ ዛቻና ማሰፈራሪያዎች ተሰንዝረዋል፡፡

እነዚህ ሁሉ በእስልምና ላይ በተለጠፉ በውስጣቸው ፖለቲካዊ ዓላማና ግብ ሸጉጠው በሚንቀሳቀሱ ቡድኖች የተፈፀሙና የታቀዱ ናቸው፡፡ የሕገወጥ ድርጊቶቹና ዕቅዶቹ መነሻ በሳኡዲ አረቢያ መንግስትና እስላማዊ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ነን በሚሉ ተቋማት የገንዘብ ድጋፍ የሚመሩ የወሃቢ ሰለፊ የአክራሪነት እንቅስቃሴ ናቸው፡፡

ይህ በተለያየ ስያሜ በተለይ የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች በሚበዙባቸው የአገሪቱ አካባቢዎች ውስጥ ውስጡን በሕቡእ ሲካሄዱ የቆዩ የፖለቲካ ዓላማ ያላቸው የወሃቢ ሰለፊ የአክራሪነት እንቅስቃሴዎች በ2004 ዓ/ም አጋማሽ ላይ በአዲስ አበባ ኢትዮጵያዊያን በሙሉ ሊያዩትና ሊያዳምጡት በሚችሉበት ደረጃ አደባባይ ለመውጣት በቅቷል፡፡

የሰለፊ ወሃቢ የአክራሪነት እንቅስቃሴውን አደባባይ ይዘውት የወጡት 1 ሺህ 500 ያህል ሰዎች በአወሊያ መስጊድ ውስጥ ተሰባስበው እርስ በርስ በመመራረጥ " የሙስሊሙ መፍትሄ አፈላላጊ ኮሚቴ" ብለው ራሳቸውን በሰየሙ አስራ ሰባት ያህል ግለሰቦች ነው፡፡

እነዚህ በአወሊያ መስጊድ ውስጥ እርስ በርስ ተመራርጠው " የሙስሊሙ የመፍትሄ አፈላላጊ" በሚል የተደራጁ ግለሰቦች "መንግስት ምላሽ ሊሰጥበት የሚገባቸው ጥያቄዎች አሉን" በማለት አቤቱታ አቅርበው አደባባይ ወጡ፡፡ በኢፌዴሪ ሕገመንግስት መሰረት ሃይማኖትና መንግስት ፍፁም የተለያዩ በመሆናቸው፣ መንግስት ሃይማኖታዊ ጉዳይ ውስጥ የመግባት ስልጣን ባይኖረውም "የሙስሊሙ መፍትሄ አፈላላጊ ነኝ" ያለው ቡድን መንግሰትን ካላነጋገርኩ ሞቼ እገኛለሁ ይላል፡፡

ይሄኔ ሃይማኖት እንደ ሕዝብ ማህበራዊ ጉዳይ የዜጎች ጉዳይ በመሆኑ መንግስትን የሚመለከትበት አግባብ ስላለ፣ እንዲሁም ማንኛውም ዜጋ በማንኛውም ጉዳይ ላይ በደል ተፈጽሞብኛል ብሎ አቤቱታ የማቅረብና የመደመጥ መብት ስላለው መንግስት በፌደራል ጉዳዮች ሚኒስቴር በኩል አስራሰባቱን ግለሰቦች ተቀበላቸው፡፡ ቡድኑ ለፌደራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ጥያቄዎቹን አቀረበ፡፡

በቡድኑ ከቀረቡት ጥያቄዎች መሃከል መሰረታዊዎቹና አክራሪው ቡድን የተንጠለጠለባቸው ሶስት ናቸው፡፡ እነዚህ ጉዳዮች በተደጋጋሚ ተነስተው በተለያዩ ግለሰቦች በቃልና በፅሁፍ ማብራሪያ የተሰጠባቸው ቢሆንም አሁንም ድረስ በውጭና በአገር ውስጥ ያሉ የአክራሪው ቡድን ጀሌዎች ሙጭጭ ብለው የተንጠለጠሉበት በመሆኑና ሕጋዊ ከለላ ይሆነናል ብለው የያዙት በመሆኑ መልሶ ማስታወሱን ተገቢ ሆኖ አግኝቼዋለሁ፡፡

እነዚህ ጥያቄዎች በወቅቱ በስራ ላይ የነበረው የእስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤ/ት ወይም መጅሊስ አባላት ወርደው በምትካቸው ሌሎች እንዲመረጡ፣ መስጊድን ጨምሮ ትምህርት ቤትና መሰል ማህበራዊ አገልግሎት መስጫዎች ያሉት አወሊያ ተቋም የባለቤትነት መብት ለሙስሊሙ ማሕበረሰብ ይሰጥ፣ አሕባሽ የተባለ መጤ የእስልምና አስተምህሮ እየተሰጠ በመሆኑ ይህ እንዲቆም የሚሉ ናቸው፡፡ የፌደራል ጉዳዮች ሚኒስቴር

ሚኒስትርና ሌሎች ከፍተኛ ባለስልጣናት በእነዚህ ጉዳዮች ዙሪያ ከቡድኑ ጋር ተወያይቶ መግባባት ላይ ደርሶ ነበር፡፡

በዚህ ውይይት ላይ የእስልምና ምክር ቤት (መጅሊስ) አባላትን ምርጫ በተመለከተ ጥያቄው ተገቢ መሆኑን የገለጹት የፌደራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ባለስልጣናት፣ ሆኖም ጉዳዩ ሙስሊሙን ሕብረተሰብ ብቻ የሚመለከትና ከመንግስት ስልጣን ውጭ በመሆኑ፣ ጸጥታን ማስከበርና አዳራሽ የመሳሰሉ ሁኔታዎችን ድጋፍ ከማድረግ ያለፈ በጉዳዩ ውስጥ ጣልቃ የመግባት ስልጣን እንደሌለው አስታውቀ፡፡ በዚሁ የምክር ቤቱ (የመጅሊሱ) ምርጫም እንዲካሄድ መግባባት ላይ ተደረሰ፡፡

አወሊያ መስጊድ ውስጥ እርስ በርስ ተመራርጠው "የሙስሊሙ ተወካይ" ነን ያሉት ግለሰቦች፣ በስራ ላይ በነበረው የእስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ላይ እምነት ስላልነበራቸው፣ ምርጫውን በገለልተኝነት  አያካሂድም የሚል አቋም ነበራቸው፡፡ በዚሁ መሰረት ጉዳዩ የሚመለከተውና በገለልተኝነት ሊመራው የሚችለው  አካል የእስልምና ሃይማኖት ሊቃውንት (ኡላማዎች) ጉባኤ በመሆኑ ምርጫውን እንዲያስፈጽም መግባባት ላይ ይደረሳል፡፡

በዚሁ መሰረት የኡላማዎች ጉባኤ ለወራት ያህል ዝግጅት ሲያደርግ ከቆየ በኋላ በ2005 ዓ/ም መስከረም ወር ላይ የእስልምና ጉዳዮች ምክር ቤት አባላት ምርጫ ተካሄደ፡፡ በምርጫው ላይ 8 ሚሊየን ያህል ለአካለ መጠን የደረሱ ሙስሊሞች ተሳትፈዋል፡፡ ምርጫው  ከአንድ ሳምንት በፊት በቀጥታ የድምፅ አሰጣጥ አስመራጭና የምርጫ ታዛቢ በመምረጥ ነበር የተጀመረው፡፡ አስመራጮችና የምርጫ ታዛቢዎች በተመረጡ በሳምንቱ በመላው አገሪቱ በቀበሌ ደረጃ አዲስ አበባ የቀበሌ መዋቅር ስለሌለ በወረዳ ደረጃ የመጅሊሰ አባላት ምርጫ ተካሄደ፡፡ ምርጫው በቀጥታ የድምፅ አሰጣጥ ስርአት የተከናወነና የድምፅ ውጤቱም እዛው የተገለፀ በመሆኑ ተአማኒነቱ ምንም የሚያጠራጥር አልነበረም፡፡

በዚህ አኳኋን በመላው ኢትዮጵያ በቀበሌ፣ በአዲሰ አበባ ደግሞ በወረዳ ደረጃ የተመረጡት የሙስሊሙ ተወካዮች ተሰብስበው የወረዳ፣ የዞንና የክልል በመጨረሻም ከየክልሉ ተመርጠው የተወከሉት ክልላዊ የእስልምና ጉዳዮች ምክር ቤት አባላት አገራዊ የእስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት አባላትንና አመራሮችን ሰይመው አዲሱ መጅሊስ በይፋ ስራውን ጀመረ፡፡

ቡድኑ በሁለተኛ ደረጃ ያነሳው ጥያቄ “አሕባሽ” የተሰኘው የእስልምና ሃይማኖት አስተምህሮ መስጠት ይቁም የሚል ነው፡፡ የፌደራል ጉዳዮች ሚኒስቴር በዚህ ጉዳይ ላይ በሰጠው ምላሽ፣ ምን አይነት አስተምህሮ መቼና በማን መሰጠት አለበት የሚለውን መወሰን የመንግስት ጉዳይ ሳይሆን የእስልምና ሃይማኖት የበላይ መሪ የሆነው የመጅሊሱ ስልጣን መሆኑን አሳውቋል፡፡ ከዚሁ ጋር አያይዞ ማንኛውም ዜጋ የፈቀደውን ሃይማኖትና እምነት የመከተል ሕገመንግስታዊ መብት ስላለው የተጠቀሰውን አስተምህሮ በሰላማዊ መንገድ መከተል የሚፈልጉ ካሉ መከልከል እንደማይቻልም አስታውሷል፡፡ እርግጥ ሰበካው በግዳጅ እየተሰጠ ከሆነ ይህ ተገቢ ባለመሆኑ እንዲጣራ እንደሚደረግም አስታወቀ፡፡ በነገራችን ላይ ከእስልምና ሃይማኖት ሊቃውንት መረዳት እንደተቻለው አህባሽ የሚባል የእስልምና አስተምህሮ የለም፡፡ አሕባሽ የሚለው ስያሜ ከኢትዮጵያ ወደሳኡዲ አረቢያ ሄደው በዚያ ነባሩን የኢትዮጵያ የእስልምና ስርአት ያስተምሩ ለነበሩ ኢትዮጵያዊ ኡላማ አስተምህሮ በዋሃቢ ሰለፊ የተሰጠ ስያሜ ነው፡፡

በሳኡዲ አረቢያ በዋሃቢ ሰለፊዎቸ “አህባሽ” የሚል ስያሜ የተሰጠውንና የአወሊያው ቡድን “ከአገር ይጥፋልኝ” ያለውን አስተምህሮ ጉዳይ እንዲያጣራ በጉዳዩ ላይ ጥልቅ እውቀት ያላቸው የእስልምና ሊቃውንት (ኡላማዎች) ያካተተው ጉባኤ ሃላፊነት ተሰጠው፡፡ የኡላማዎቹ ጉባኤ ማጣራቱን አከናውኖ አንድም ቦታ በግዳጅ የሚሰጥ ሰበካ አለመኖሩን፣ አሕባሽ የተባለ አዲስ አስተምህሮ መጣብን የተባለውንም በተመለከተ ኢትዮጵያ ውስጥ ከሺህ አመታት በላይ ሲሰበክ ከቆየው አሕለል ሱና አስተምህሮ የተለየ አንዳችም የተለየ አስተምህሮ እንዳልተሰበከ በይፋ ምስክርነት ሰጠ፡፡

ቡድኑ አንስቶት የነበረው ሶስተኛ ጥያቄ “አወሊያ ተቋም የሙስሊሙ ተቋም ስለሆነ ለሙስሊሙ ይመለስ” የሚል ነበር፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ በተደረገ ውይይት እርግጥም ተቋሙ የሙስሊሙ ሕብረተሰብ በመሆኑ ዙሪያ መግባባት ላይ ተደርሷል፡፡ ተቋሙ የሙስሊሙ በመሆኑ የኢትዮጵያ እስልምና ሃይማኖትን በበላይነት ለመምራት በሙስሊሙ ውክልና በተሰጠው የእስልምና ጉዳዮች ምክር ቤት (መጅሊስ) ስር ሆኖ ሕዝብ የወከላቸው አባላት በተካተቱበት ኮሚቴ እንዲተዳደር ስምምነት ላይ ተደርሷል፡፡አሁን ተቋሙ በዚህ አኳኋን እየተዳደረ ይገኛል፡፡

በአወሊያ መስጊድ ራሱን የሙሰሊም ተወካይ አድርጎ የሰየመው ቡድንና ጀሌዎቹ ግን ይህን መቀበል አልፈለጉም፡፡ እነርሱ የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ሃይማኖታዊ ጉዳይ ዋና ጉዳያቸው ስላልሆነ ተቋሙ 8 ሚሊየን ሙስሊሞች በወከሉት መጅሊስ ስር ሆኖ በኮሚቴ እንዲተዳደር መወሰኑን አልተቀበሉትም፡፡ የእነርሱ ፍላጎት ከሳኡዲ አረቢያ በሚፈስ በሚሊየን የሚቆጠር ፔትሮ ዶላር በአክራሪነት የተቃኘ አስተምህሮ የሚሰጥበትና በሃያ አመታት ግዜ ውስጥ ኢትዮጵያ ውስጥ

እስላማዊ መንግስት የመመስረት ራዕያቸውን የሚያስፈጽሙበት ማእከል ማደረግ ነው፡፡ ውሳኔውን ያለተቀበሉት በዚህ ምክንያት ነው፡፡

እንግዲህ ከላይ የተገለጸው ራሱን የሙስሊሙ ተወካይ አድርጎ ሰይሞ ሲንቀሳቀስ የነበረው ቡድን ባነሳቸው ጥያቄዎች ዙሪያ ከመንግስት ከፍተኛ ሃላፊዎች ጋር ተወያይቶ ጉዳዮቹ እልባት የተበጀላቸው መሆኑን ያመለክታል፡፡

ቡድኑ ግን ላነሳቸው ጉዳዮች የተሰጠው ምላሽ፣ ከውጭ በሚፈስለት ፔትሮ ዶላር የረጅም ግዜ የፖለቲካ ገቡን ማራመድ ስለማያስችለው፣ ለግዜው ሌላ አመቺ አጀንዳ ማንሳትም ስላልቻለ እስካሁን በጀሌዎቹ አማካኝነት ስልመጅሊስ ምርጫ፣ አህባሽ በሚል ስለሚጠራው አስተምህሮና ስልአወሊያ ተቋም ማውራቱን አላቋረጠም፡፡

ቡድኑ ላነሳቸው ጥያቄ በውይይት እልባት በተበጀ ማግስት ባለፈው አመት ሃምሌ ወር ላይ ሁከት ወደመቀሰቀስ ተሸጋግሮ ነበር፡፡ በዚህ ወቅት በአዲስ አበባ የአፍሪካ ሕብረት የመሪዎች ጉባኤ በተካሄደበት ወቅት አጋጣሚውን ለሁከት ለመጠቀም ከየክለሉ ደጋፊዎቹን ወደአዲስ አበባ እንዲሰባሰቡ ጥሪ በማስተላለፍ ሕገ ወጥ ሕዝባዊ ስብሰባ ጠርቶ ነበር፡፡

ይህን ስብሰባ ጠርቶ በነበረበት ዋዜማ የእስልምና ሃይማኖት ስርኣት ከሚያዘው ውጭ እኩለሌሊት ላይ ሁለት ሶስት በሚሆኑ የአዲስ አበባ መስጊዶች ሃዛን ለፍፈው ጥቂት ደጋፊዎቻቸው በሌሊት ከቤት እንዲወጡ አድርገዋል፡፡ በዚህ ጥሪ መሰረት በሌሊት የወጉት ደጋፊዎቻቸው ሁከት ለመፍጠር ሞክረው እንደነበርም ይታወሳል፡፡ በዚህ የሁከት እንቅስቃሴ ላይ አዋኪዎቹ የሰላማዊ ሙስሊሞች ግቢና ቤት በር እየደበደቡ “ጀሃድ ነው ውጡ ! ” በማለት የአመፅ ቅስቀሳ ሲያስተላልፉ እንደነበርም እናስታውሳለን፡፡ ፀጥታ በማስከበር ስራ ላይ በተሰማሩ ፖሊሶችም ላይ ጉዳት ለማድረስ ተሞክሯል፡፡ በማግስቱ በአንዋር መስጊድ አካባቢ በሕዝብና በግለሰቦች ንብረት ላይ ድንጋይ በመወርወር ጉዳት ያደረሰ ሁከት ተቀስቅሶ እንደነበርም እናስታውሳለን፡፡

ይህን ሃይማኖትን ሽፋን ያደረገ ሁከት ተከትሎ አብዛኞቹ ራሳቸውን “የሙስሊሙ መፍትሄ አፈላላጊ” ብለው የሰየሙ ገለሰቦች ሁከቶቹን በመጠንሰስና በመመራት ወንጀል ተጠርጥረው በቁጥጥር ስር ዋሉ፡፡ ግለሰቦቹ በሁከት መንግስትንና ሕዝብን በማስፈራራት ለማንበርከክ የሽብርተኝነት ወንጀል ለመፈጸም በመንቀሳቀሰ ወንጀል በፍርድ ቤት ክስ ተመስርቶባቸዋል፡፡ በአሁኑ ወቅት የተጠርጣሪዎቹ ጉዳይ በፍርድ ሂደት ላይ ይገኛል፡፡

ከዚህ በኋላ አክራሪው የአወሊያ ቡድን የቀፈቀፋቸው ጀሌዎች ተጨማሪ የሁከት አጀንዳ ይዘው ብቅ አሉ ፡፡ ይህም ከፍርድ ቤት ውሳኔ ውጭ "የሙስሊሙ ተወካዮች ይፈቱ" የሚል ነው፡፡ ማን እንደወከላቸው የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ባያውቁም "የሙስሊሙን ተወካዮች ማሰር ሙስሊሙን ማሰር ነው ምንትስ ቅብጥርስ" ማለታቸውንም ታዝበናል ፡፡